ቀን/Dat 09/08/2017 ዓ.ም
ቁጥር/Ref.No ደ/ኢ/ጠ/ፍ-ዐ12-514

ለ12ቱም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት

ባሉበት

ጉዳዩ፤የጸደቀ መመሪያ መላክን ይመለከታል።

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የክልሉን ፍርድ ቤቶች የችሎት ስርዓት መመሪያን አፅድቋል።

በመሆኑም የክልሉን ፍርድ ቤቶች የችሎት ስርዓት መመሪያ ቁጥር 04/2017 ዓ.ም ሥራ ላይ እንዲውል እንዲደረግ እያሳሰብኩ የፀደቀውን መመሪያ የያዘ 20 ገጽ ከዚህ ሸኚ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላክን መሆኑን አሳውቃለሁ።

ከሠላምታ ጋር //

ቦጋለ ፈይሳ ወ/ጊዮርጊስ
የጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት

ግልባጭ

- ✓ ለክቡር ፕሬዚደንት ጽ/ቤት
- ✓ ለክቡር ምክትል ፕሬዚደንት ጽ/ቤት
- ✓ ለዋና ጉባኤ ጽ/ቤት
- ✓ ለአቤቱታ መስማት መወሰን ዋና ስራ ሂደት
- ✓ ለተከላካይ ጠበቆች ጽ/ቤት

ጠ/ፍ/ቤት

ሳዉላ


Tel 0467771865 Fax 0467771642 p.Box 98

የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት

THE SOUTH ETHIOPIAN REGIONAL STATE

# የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የክልሉ ፍርድ ቤቶች የችሎት ስርዓት መመሪያ ቁጥር 04/2017

ሚያዚያ 07 ቀን 2017 ዓ.ም

የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ሳዉላ

# የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ፍርድ ቤቶች የችሎት ስርዓት መመሪያ ቁጥር 04/2017

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግሥት የዳኝነት ስልጣን ለፌዴራልና ለክልል ፍርድ ቤቶች የተሰጠ ከፍተኛ ኃላፊነት በመሆኑ ይህንን ኃላፊነት ከፍተኛ ስነ-ምግባር የተላበሰ ተቋማዊ ባህልን መገንባት እና መተግበር በማስፈለጉ፣ በፍርድ ቤቶች እስካሁን የችሎት ስርዓት መመሪያ ባለመኖሩ፣ ወጥነት እና ግልጽነት የጎደለው የችሎት ስርዓት አሰራር መከተል አለመቻሉን ከግምት በማስገባት፣

ፍርድ ቤቶች የችሎትን ስርዓት በሚጥሱ የፍ/ቤት ተገልጋዮች ላይ በዳኞች የሚሰጠው ቅጣት ወጥነት ያልነበረው በመሆኑ ወጥነት እና ተገማችነት እንዲኖረው ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

ዳኞች፣ ተከራካሪ ወገኖች፣ ተገልጋዮች፣ የችሎት ታዳሚዎች የፍርድ ቤቱ ማህበረሰብ እንዲሁም ሌሎችም የችሎት ሥርዓት እና አካሄድ እንዲያውቁ፣ እንዲያከብሩ፣ እንዲያስከብሩ እና እንዲመሩበት ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፣ የችሎት ስርዓት በማክበር እና በማስከበር የህብረተሰቡን በፍርድ ቤት ላይ ያለውን አመኔታ ለማረጋገጥ፣የክልሉ ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 06/2016 አንቀጽ 66/2/ መሠረት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይሁን ይህንን የክልሉ ፍርድ ቤቶች የችሎት ስርዓት መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ "የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ፍርድ ቤቶች የችሎት ስርዓት መመሪያ ቁጥር 04/2017 ተብሎ ሊጠራ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም ካላሰጠው በስተቀር በዚህ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ፍርድ ቤቶች የችሎት ስርዓት መመሪያ ውስጥ፡-

1.ፍርድ ቤት"ማለት በክልሉ ሕገ-መንግሥት መሠረት የተቋቋመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣የወረዳ ወይም የከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ማለት ነው፡፡

2. "ዋና ጉባዔ" ማለት በጠቅላይ ፍርድ ቤት ደረጃ የተቋቋመ የዳኞች አስተዳደር ዋና ጉባኤ ማለት ነው፡፡

3."የፍርድ ቤት አመራር" ማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፣የወረዳ ወይም የከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንቶችና ምክትል ፕሬዚዳንቶች በፍርድ ቤቶች እና በዳኞች አስተዳደር አዋጅ መሰረት በኃላፊነት የተጠቀሱትን ማለት ነው፡፡

4."ዳኛ" ማለት በክልሉ የዳኝነት አስተዳደር ዋና ጉባኤ አቅራቢነት የዳኝነት ተግባራትን እንዲያከናዉን በክልሉ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተሾመ ነዉ፡፡

5."የጉባዔ ተሿሚዎች" ማለት በክልሉ የዳኝነት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 07/2016 አንቀጽ2/15/ መሠረት በዳኞች አስተዳደር ጉባዔ የሚሾም ሰው ማለት ነው፡፡

6."አስተዳደር ሠራተኛ" ማለት ከዳኛና ከዳኝነት አስተዳደር ጉባዔ ተሿሚ ዉጭ ያለ ማንኛዉም የፍድ ቤት ሠራተኛ ማለት ነው፡፡

7."ችሎት"ማለት ዳኛ ወይም ዳኞች ጉዳዮችን የሚያከራክሩበት፣ ምስክሮች የሚሰሙበት፣ የዳኝነት አገልግሎቶች የሚሰጡበት እንዲሁም ውሣኔ የሚያነቡበት የችሎት ማስቻያ ቦታ፣ ስፍራ ወይም ቤት ማለት ነው፡፡

8."የችሎት ፖሊስ" ማለት የችሎት ስርዓት እንዲያስከብር ከሚመለከተው የክልል ፣ የዞን ፣ወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር የፖሊስ ተቋም የተመደበ ፖሊስ ወይም ሰው ማለት ነው፡፡

9."የችሎት ስርዓት አስከባሪ" ማለት በፍርድ ቤቱ የሚተዳደር የችሎት ስርዓት የሚያስከብር ሠራተኛ ማለት ነው፡፡

10."አቃቤ ሕግ" ማለት በክልሉ ፍትህ ቢሮ ማቋቋሚያ ህጎች መሠረት አቃቤ ህግ ተብሎ የተሾመ ሲሆን የፌደራል ዐቃብያነ ህግንም ይጨምራል፡፡

11."ጠበቃ" ማለት የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ለመስጠት ስልጣን ካለው አካል ፈቃድ ያገኘ የህግ ባለሙያ ሲሆን እንደ አስፈላጊነቱ የግል ድርጅቶች፣ የልማት ድርጅቶች እንዲሁም

ሌሎች የመንግሥት መስሪያ ቤቶችን ወክሎ የሚከራከር ነገረፈጅ ሆኖ የመከላከያና የክልል ፖሊስ ነገረፈጅ እንዲሁም ተከላካይ ጠበቆችንም ይጨምራል፡፡

12.አስተርጓሚ``ማለት የሀገር ዉስጥ ፤የዉጭ ቋንቋ እና የምልክት ቋንቋ በብቃት መስማትና መናገር የሚችልና የክልሉን መንግስት የሥራ ቋንቋ የሚችል ሆኖ ይህን የማስተርጎም አገልግሎት የሚሰጥ ሰዉ ማለት ነዉ፡፡

13.ባለ ጉዳይ ማለት እየተካሄደ ባለ ክርክር ዉስጥ የሚሳተፍ እንደ ከሳሽ፤ ተከሳሽ፤ አመልካች ዐቃቢያነ ህግ፡ ጠበቃ፤አቤቱታ አቅራቢ፤ተጠሪ፤የክርክር ጣልቃ ገብ፤ዉሳኔ ለመቃወም ወደ ክርክር የገባ ወይም ይግባኝ ባይ እና መልስ ሰጪ ሆነዉ ችሎት ላይ የቀረበ ወይም ማንኛዉም የፍርድ ቤት ተገልጋይ ማለት ነዉ፡፡

14.ምስክር` ማለት በክስ ወይም መልስ ላይ የተዘረዘረ ወይም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ችሎት ላይ ቀርቦ የምስክርነት ቃሉን የሚሰጥ ሰዉ እና የባለሙያ ምስክርን ይጨምራል፡፡

15.`ፖሊስ` ማለት የማረሚያ ቤት ፤ የክልል ፤የፌዴራል ፡ የጉምሩክ መስሪያ ቤት እና ትራፊክ ፖሊስን ይጨምራል፡

**3. የጾታ አገላለፅ**

በዚህ መመሪያ ማንኛዉም በወንድ ጾታ የተገለፀዉ አነጋገር የሴት ጾታንም ያካትታል፡፡

**4.የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ በክልል ፍርድ ቤቶች በችሎት ሂደት ዉስጥ በምሳተፍ፤ በተለይም በችሎት ሂደት ዉስጥ በሚሳተፍ ማንኛዉም ሰዉ በተለይ ዳኛ፤ የጉበኤ ተሿሚ ተከራካሪ፤ ምስክር፤ አስተርጓም፤የፍርድ ቤት የአስተዳደር ሰራተኛ፤ የችሎት ሥነ-ስርዓት አስከባሪ ፖሊስ፤ የፍርድ ቤት የችሎት ሥነ- ስርዓት ሰራተኛ ፤ የችሎት ፤ ታዳሚ፤ፖሊስ፤ዓቃቤ ህግ፤ ጠበቃ ወይም ከችሎት ዉጪ በፍርድ ቤት ቅጥር ግቢ በሚገኝ ማኛዉም ሰዉ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል ፡፡

22.ከሬጅስትራር እና ከፍ/ቤቱ አስተዳደር ሰራተኞች የሚጠበቅ ስነ-ምግባር

1.ለችሎቱ በቂ ድጋፍ የሚሰጡ የአስተዳደር ሰራተኞች መመደብና በማንኛዉም ሁኔታ ሲጓደል ችሎት ከመጀመሩ በፊት ማሟላት፤

2. በእለቱ የተቀጠሩ መዛግብን ከቀጠሮ ቀን በፊት ለዳኛ አሟልቶ ማቅረብ፤

3. የችሎትን ሥራ ሳያደናቅፉ ወይም ሳያዉኩ መስራት፤

4. እርስ በእርስም ሆነ ባለጉዳዮችን በማክበር በአግባቡ ማስተናገድ፤

5. በዳኛዉ የሚሰጠዉን ትዕዛዝ ማክበር፤መቀበል እና በተገቢዉ ጊዜ በስራ ላይ ማዋል፤

6. ለችሎቱ ሥራ እጅግ አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር ክርክር እየተካሄ ዳኛዉን፤ተከራካሪ ወገኖችን፤ምስክሮችን ወይም ከማንኛዉም ሰዉ ጋር ችሎት ላይ ለማዉራት፤

7. የፍ/ቤቱን መዝገብ እና ሰነዶች በአግባቡ መያዝ፤ በወቅቱ ለችሎቱ ማቅረብ፤

8. ከችሎቱ ጋር በተያዘ አስተዳደራዊ ጉዳዮች የሚመለከታቸዉ አስተዳደር ሰራተኞች ኃላፊነታቸዉን ስለመወጣታቸዉ መከታተል፤

9. ለችሎቱ የሚያስፈልጉ ግብአት መሟላታቸዉን መከታተልና እንዲሟሉ ማድረግ፤

10. የመዝገቡን ሚስጥር መጠበቅ ማንኛዉንም አይነት ማስረጃ ወይም ጽሑፍ ከችሎቱ ፍቃድ ዉጪ ከመዝገቡ ጋር እንዳይያያዝ ማድረግ፤

11. በዚህ መመሪያ የተገለፀዉ እንደተጠበቀ ሆኖ በጉባኤ ተሿሚዎች እና በአስተዳድር ሰራተኞች መተዳደሪያ ደንብ የተደነገጉ ኃላፊነትና ግዴታቸዉን መፈፀም አለባቸዉ፡፡

23. የቋንቋ አስተርጓሚ ኃላፊነትና ተግባር

1.ቋንቋ የመተርጎም አገልግሎት በአግባቡ ማካሄድ፤

2. ባለጉዳዮችን ማክብር እና በአግባቡ ማስተናገድ፤

3. ያለአድልኦ ትክክለኛዉን ትርጓሜ ማስተላለፍ፤

4.የዳኛዉን ትዕዛዝ ማክበር፤መቀበል እና መተግበር፤

## ክፍል ሁለት

## የክልል ፍርድ ቤቶች የችሎት ስርዓት ዓላማና ግብ

**5.ዓላማ**

የችሎት ስርዓት መመሪያ ዓላማ በህግ ለፍርድ ቤቶች የተሰጠ ስልጣንን በአግባቡ ለመተግበር እና ተገልጋዩም የችሎት ስርዓትን በመረዳት ለፍርድ ቤት እና ለችሎት ያለዉን ክበረታ ለማረጋገጥ እና ተቋማዊ የአሰራር ባህልን መገንባት ነዉ፤

**6.ዝርዝር ዓላማ**

**የችሎት ስርዓት መመሪያ ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸዉ**

1.ፍርድ ቤቶች እና ችሎቶች የሚመሩበትን ስርዓት መዘርጋት፤

2.ዳኞች፤የጉባኤ እና የአስተዳደር ስራተኞች ከፍተኛ ስነ ምግባር በመታነፅ ተቋማዊ ባህል መገንባት፤

3.ወጥነት እና ግልጽነት ያለዉ የችሎት ስርዓት እንዲኖር ማስቻል፤

4. የችሎት ስርዓትን ዳኞች፤ ተከራካሪ ወገኖች፤የችሎት ታዳሚዎች እንዲያዉቁና እንዲማሩበት ማድረግ፤

5.የህብረተሰቡን አመኔታ ማረጋገጥ፤

## ክፍል ሶስት

## ቅድመ ችሎት ስርዓት

**7.የቅድመ ችሎት ስርዓት**

1.ችሎት ከመጀመሩ በፊት የችሎት ዉሎ ፕሮግራምን የሚያመላክት እንዲሁም በእለቱ የተቀጠረ መዝገብ ቁጥር ፤የተቀጠረበት ሰዓት፤የባለ ጉዳዮችን ስም፤የጉዳዩን አይነት እና ጉዳዩ የተቀጠረበት ምክንያት የሚያመለክት በማስታወቂያ ሰሌዳ ወይም በቴሌቪዥን ማሳያ በግልጽ ቦታ መለጠፍ ወይም መዘጋጀት አለበት።

2.የችሎቶች፤ የዳኛ ቢሮ፤ የሬጅስትራር ቢሮ፤የመረጃ ዴስክ፤የአስተዳደር ሰራተኞች ቢሮ ስያሜ ለባለጉዳዮች በሚታይ መልኩ በፅሁፍ መገለፅና በየበሩ መለጠፍ አለበት።

3.ችሎት ከመጀመሩ በፊት ሬጅስትራሮች፤ ባለሙያዎች እንዲሁም ጉዳዩ የሚመለከታቸዉ የፍርድ ቤት ሰራተኞች ችሎቱ ስለመፅዳቱ ማረጋገጥ፤ በችሎት አዳራሽ መብራት ፤ የእለቱ መዝገብ ፤ የዳኛ አጀንዳ፤የዳኞች ስም ያለበት የጠርጴዛ ባጅ፤ አዋጆችና ህግ መጻሐፍት፤ የችሎት ወረቀት፤ብዕር፤የድምጽ መቅረጫ፤ የችሎት መዶሻ እንዲሁም በችሎት መሟላት ያለባቸዉ በሙሉ ስለመሰናዳታቸዉ ማረጋገጥ አለባቸዉ

**9.ባለ ጉዳዮች የሚስተናግዱባቸዉ ቅደም ተከተል**

ዳኛዉ ጉዳዮችን በጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር መመሪያ መሰረት በመቅጠር፣ ቅድሚያ ሊሰጣቸዉ የሚገቡ ጉዳዮችን በጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር መመሪያ መሰረት ማስተናገድ አለበት፡፡

**10.የቃለ መሐላ ስርዓት**

1.ዳኛዉ ወይም የፍርድ ቤቱ አስተዳደር ሰራተኛ የቃለ መሀላዉን ዓላማ እና ዉጤት በማስረዳት አግባብነት ባላቸዉ የወንጀል እና የፍትሐብሔር ሥነ- ስርዓት ድንጋጌዎች መሰረት ቃለ መሀላ ማስፈፀም አለበት፡፡

2.ቃለ መሀላ ፍትህን እና እዉነትን በማዉጣት ረገድ ከፍተኛ ድርሻ ስላለዉ የመማል ግዴታ ያለበት ማንኛዉም ሰዉ ፣ተከራካሪ ወገን፣ አስተርጓሚን ጨምሮ በአግባብ መማል አለበት፡

3.ቃለ መሀላ በዳኛ ፊት ሆኖ መሀላዉ በዳኛ ወይም በፍርድ ቤቱ አስተዳደር ሰራተኛ የሚፈጸም ሆኖ ቃለ መሀላዉ በግልፅ ለችሎቱ በሚሰማ በሚችል መልኩ በተናጠል መፈፀም አለበት፡፡

**11.ለችሎት ክብር ስለመቆም**

1.በችሎት ሂደት ፍርድ፣ቅጣት፣ ዉሳኔ ወይም ብይን ሲነበብ፣ የክስ እና መልስ ቅብብል ሲደረግ፣ክርክር ሲካሄድ፣ ባለጉዳዩ ምስክሮችን ሲያሰማ፣ባለጉዳዩ አቤቱታ ሲያቀርብ፣ትዕዛዝ ወይም ዳኛዉ በያዘዉ ጉዳይ በሚያስችልበት ወቅት ጉዳዩ የሚመለከተዉ ባለጉዳይ ቆሞ መከታተል አለበት፡፡

2.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር የተደነገገዉ ቢኖርም ችሎቱ እንደየሁኔታዉ ክርክሩ የሚራዘም ከሆነ አንደኛዉ ወገን ሲናገር ሌላኛዉ ወገን ተናግሮ እስክቀመጥ፣ እንዲቀመጥ ፣ በጋራ ከተከሰሱት ወይም ከከሰሱት ሰዎች መካከል ምስክር ከሚያሰማ ወይም ከሚሰማበት ዉጪ ያለዉ ተከሳሽ ወይም ከሳሽ እንዲቀመጥ እንዲሁም በህመም ወይም እርግዝና ወይም አካል ጉዳት ምክንያት መቆም የማይችል ሰዉ እንዲቀመጥ ዳኛዉ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

**12.ድምፅን ከፍ አድርጎ ስለመናገር**

1.ዳኛ ችሎት ሲመራ ለችሎት ታዳሚዎች በሙሉ በሚሰማ መልኩ መናገር አለበት፡፡

2.ዓቃቢያነ ህጎች፤ ጠበቆች፤ ምስክሮች፤ ተከራካርዎች እና ባለ ጉዳዮች ክርክራቸዉን ሲያቀርቡ ዳኛዉ፤ችሎቱ እና ተከራካሪዉ ወገን ሊሰማ በሚችል ሁኔታ መናገር አለባቸዉ።

**13.የአለባበስ ስርዓት**

1.ማንኛዉም ዳኛ ችሎት ሲያስችል የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ዳኛ በጥቁር ካባ መደብ ላይ ከአንገት እስከ እግር ጫፍ የሚደርስ ሰማያዊ ቀለም ያለዉ ካባ እና ፤ በካባዉ በስተቀኝ በኩል ትከሻ ላይ በክብ መደብ የተሰራ ሚዛን ፤ከአንገት የሚጀምር ወርቃማ መነሳነስ እንዲሁም በሁለቱም የካባዉ እጀታ ላይ ሶስት ሰማያዊ መስመሮች ያሉት፤የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኛ ጥቁር ካባ መደብ ላይ ከአንገት እስከ እግር ጫፍ የሚደርስ ሰማያዊ ቀለም ያለዉ ካባ ፤በካባዉ በስተቀኝ ትከሻ ላይ በክብ መደብ የተሰራ ሚዛን እና ከአንገት የሚጀምር ሁለት ወርቃማ መነሳነስ እንዲሁም በካባዉ እጀታ ላይ ሁለት ሰማያዊ መስመር ያለዉ ካባ፤የወረዳ ወይም ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዳኛ በጥቁር ካባ መደብ ላይ ከአንገቱ እስከ እግር ሰማያዊ ቀለም ያለዉ ካባ እና ከአንገት የሚጀምር አንድ ወርቃማ መነሳነሰ እንዲሁም በካባዉ እጀታ አንድ ሰማያዊ መስመር ያለዉ ካባ መለበስ አለበት።

2.በዚህ አንቀፅ ንዐሰ አንቀፅ 1 የተጠቀሰዉ በወንጀል ነክ ነገር ዉስጥ ገብተዉ የተገኙ ወጣቶች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረዉም። ሆኖም የቤተሰብ፤ የሴቶችና የሕፃናት ችሎት እንዲሁም ችሎት አስከባሪዎች እንደ አስፈላጊነቱ በችሎት ካባ ሳያደርጉ ይችላሉ።

3.የክልል ዐቃቢያን ህጎች በተቋማቸዉ እዉቅና ያለዉ ካባ በችሎት ለብሰዉ መገኘታቸዉ እንደተጠበቀ ሆኖ በችሎት የሚገኝ የክልል ዓቃቤ ህግ ሙሉ ጥቁር ካባ አንገቱ ላይ ቀይ የሆነ፤ ጠበቃ ሙሉ ጥቁር ካባ ነጭ ሪቫን፤እና ተከላካይ ጠበቃ ሙሉ ጥቁርካባ አንገቱ ላይ አረንጓዴ የሆነ ለብሶ በችሎት መግባት አለበት። የካባዉ ዓይነትና ከለር ሲለወጥ ተቋሙ ለፍርድ ቤቱ ማሳወቅ አለበት።

4.በዚህ አንቀፅ ንዑሰ አንቀፅ 1 እና 2 የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛዉም ዳኛ፤ዓቃብያነ ህግ፤ ጠበቃ ከካባዉ ዉስጥ ለወንድ ሙሉ ልብስ "ሱፍ/የጨርቅ" ኮትና ሱሪ፤ሸሚዝ እና ከረባት እንዲሁም ለሴት ሙሉ ልብስ"ሱፍ/የጨርቅ" ኮትና ሱሪ ወይም ቀሚስ፤ሸሚዝ ወይም ሹራብ መልበስ እና ካባዉ እስከ አንገት ድረስ በቁልፍ ወይም በዚፕ የተዘጋ መሆን አለበት።

13.ማንኛዉም ሰዉ በሐኪም ካልታዘ በቀር አይኑ እንዳይታይ የሚያደርግ ጥቁር መነጽር አድርጎ ችሎት መግባት የለበትም፡፡

14.ዳኛ፤ የጉባኤ ተሿሚ፤ አቃብያነ ህግ ወይም ጠበቃ ማንነቱን ሊደብቅ የሚችል ኮፍያ ወይም ጥምጣም በጭንቅላት ላይ ጠምጥሞ ችሎተ መግባት የለበትም፡፡

15.ማንኛዉም ሰዉ ፊት እና አይኑን ሙሉ ለሙሉ የሚሸፍን ወይም ሰዉ እንዳያየዉ የሚያደርግ ልብስ ለብሶ ችሎት መግባት የለበትም፡

16.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 14 እና 15 የተደነገገዉ ቢኖርም ዳኛ፤ የጉባኤ ተሿሚ፤ጠበቃ እና ዐቃብያነ ህጎችን ጨምሮ በሐይማኖት ወይም በባህል ምክንያት የሚለበሱ ልብሶችን ለብሶ ችሎት መግባት ይቻላል፡፡ ሆኖም ችሎቱ የተከራካሪዎችን ወይም የችሎቱን ባለጉዳይን ማንነት ለማጣራት ወይም ለማረጋገጥ ስል የዚያን ሰዉ ክብር፤ ባህል እና ሐይማኖት በማይጋፋ መልኩ ልብሱን ከላዩ ላይ እንዲያነሳ ማዘዝ ይችላል፡፡

17.ማንኛዉም ጠበቃ ወይም ዓቃቢያነ ህግ ከችሎት ዉጪ ጋወን/ካባ በአግባቡ ለብሶ ወደ ችሎት መግባት አለበት፤ችሎት ላይ ጋዎን/ካባ ማዉለቅ እና መቀያየር የለበትም፡፡

18.ማንኛዉም ሰዉ የፍርድ ቤቱን የጉባዓ ተሿሚ እና አሰተዳደር ሰራተኞች ጨምሮ የችሎቱን ፀጥታ በድምፅ የሚያዉክ ድርጊት በችሎት ወይም በዳኞች ቢሮ/ፅ/ቤት ዉስጥ መፈጸም የለበትም፡፡

19.የተጨማደደ፣ና ንጽሕናዉን ያልጠበቀበ ካባ ለብሶ ወደ ችሎት መግባት የተከለከለ ነዉ፡፡

**14.ተንቀሳቃሽ ስልኮች ወይም በድምጽ ሊያዉኩ የሚችሉ ሌሎች ኤሌክትሮኒክሰ መሣሪያዎች**

ማንኛዉም የችሎት ታዳሚ ወይም ባለጉዳይ ተንቀሳቃሽ ሰልኮችን ወይም በድምጽ ሊያዉኩ የሚችሉ ሌሎች ኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎችን ወደ ችሎት ከመግባቱ በፊት ድምፅ እንዲያጠፉ ይገደዳል፡፡

4..ለወንጀል ችሎት አቃቢያን ህጎች፣ ጠበቆች፣ባለ ጉዳዮች፣በወንጀል የተጠረጠሩ ወይም የተከሰሱ ሰዎች እንዲሁም ሌሎች ሰዎች ችሎቱ ከመጀመሩ በፊት ወደ ችሎቱ አዳራሽ ወይም ክፍል ገብተዉ ከዳኛዉ ፊት ለፊት አቃቢያን ህጎች ከችሎቱ በቀኝ በኩል፣ ተጠርጣሪዎች በስተግራ በኩል በተዘጋጀ ሳጥን፣ተከላካይ ጠበቆች በስተግራ በኩል ከተጠርጣሪ ጎን፣ ምስክሮች ከዳኞች ከሁለት ሜትር ርቀት በላይ በተዘጋጀ ማረፊያ፣ አስተርጓሚ ከምስክሩ ወይም ከሚያስተርጉመዉ ሰዉ አጠገብ፣ የችሎት ፀሐፊ ከችሎቱ መድረክ ፊት ለፊት በተዘጋጀ ቦታ እንዲሁም ታዳሚዎች በችሎት በተዘጋጀላቸዉ ቦታ ስፍራቸዉን መያዝ አለባቸዉ፡

5.ለፍትሐብሄር ከሳሽ ከችሎቱ በስተቀኝ በኩል፣ ተከሳሽ በስተግራ በኩል በተዘጋጀ ቦታ፣ጠበቃ በስተግራ ወይም በስተቀኝ ወክሎ በሚከራከረዉ ሰዉ ጎን፣ ምስክሮች ከዳኞች ከሁለት ሜትር ርቀት በላይ በተዘጋጀ ማርፊያ፣ አስተርጎሚ ከምስክሩ ወይም ከሚያስተርጉመዉ ሰዉ አጠገብ፣ የችሎት ፀሀፊ ከችሎቱ ሰቴጅ ፊት ለፊት በተዘጋጀ ቦታ እንዲሁም ታዳሚዎች በችሎቱ በተዘጋጀላቸዉ ቦታ ስፍራቸዉን መያዝ አለባቸዉ።

6.በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 4 እና 5 የተደነገገዉ ስርዓት ከተፈጸመ በኋላ የችሎት ስርዓት አስከባሪዉ ወይም የችሎቱ ፖሊስ በችሎቱ አዳራሽ ዉስጥ የተገኙትን ሰዎች በሙሉ ዳኞች ወደ ችሎት ሲገቡ ተነስተዉ እንዲቀበሏቸዉ በማሳሰብ ከዳኞች ፅህፈት ቤት በመሄድ ከእነርሱ ቀድመዉ ችሎት በማስገባት፣ የመቀመጫቸዉ ቦታ ሲደርሱ ለዳኞች ወታደራዊ የአክብሮት ሰላምታ በመስጠት፣ ችሎት ዉስጥ ወዳሉት ሰዎች በመዞር እነርሱንም በምልክት ሰላምታ ጠይቆ እንዲቀመጡ ማድረግ አለበት

## ክፍል አራት

## የችሎት ስርዓት

**8.የችሎት አጀማመር ስርዓትና ሰዓት**

1.የመንግስት መደበኛ የስራ ሰዓት እንተጠበቀ ሆኖ የችሎት ስራ ጠዋት 3:30 እና ከሰዓት በ8:00 መጀመር አለበት።

2.የአየር ሁኔታ ፀባይ በተለየ ሊታዩ የሚገባቸዉ እንደአካባቢዉ ነባራዊ ሁኔታ ሊቀያየር ይችላል።

3.ዳኛዉ በችሎት መደሻ በመምታት ችሎቱ ስለመጀመሩ ማብሰር አለበት።

5.ማንኛዉም ነገረፈጅ ለወንድ ሙሉ ልብስ ኮትና ሱሪ፤ሸሚዝ፤ ከረባት እንዲሁም ለሴት ሙሉ ልብስ "ሱፍ/ጨርቅ" ኮትና ሱሪ ወይም ቀሚስ፤ ከዉስጥ ሸሚዝ ወይም ሹራብ መልበስ አለባቸዉ፡፡

6.በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 4 እና 5 የተገለፀዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛዉም ዳኛ፤የጉባኤ ተሿሚ፤ዓቃብያነ ህግ፤ጠበቃ ቁምጣ፤ ጅንስ፤ የተቀደደ ልብስ፤ ቲሸርት፤የተለያዩ ፅሁፎች ያለባቸዉን አልባሳት፤ሲሊፐር ወይም ሸበጥ ጫማ መልበስ የተከለከለ ነዉ፡

7.ማንኛዉም ዳኛ፤ ረዳት፤ጠበቃ፤ዐቃቢያነ ህግ ለወንድ በጣም የረዘመ፤ ድሬድ/ራስታ ፀጉር፤ለሴት እይታን የሚከለክል የፀጉር አሰራር እንዲሁም ክፍያ ማድረግ የለበትም/የለባትም፡፡

8.የችሎት ፖሊስ ለዚህ ስርዓት የሚዉል የደንብ ልብስ እንዲሁም የችሎት አስከባሪ መሆኑን የሚያሳይ መለያ መልበስ አለበት፡፡

9.ለሬጅስትራር፤ የችሎት ስነ ሰርዓት አስከባሪ፤ድምፅ ቀራጭ እንዲሁም በችሎት ያሉ የፍርድ ቤቱ ስራተኞች የችሎቱን ክብር የሚመጥን በጠቅላይ ፍርድ ቤት በተዘጋጀ የደንብ ልብስ እና በጥቅማ ጥቅም መምሪያ መሠረት በፍርድ ቤቱ ወጪ የተዘጋጀ የደንብ ልብስ ወይም ጋዋን መልበስ አለባቸዉ፡፡

10.የፍርድ ቤቱ አስተዳደር ሰራተኞች የተለየ የአለባበሰ ስርዓት እንዲከተሉ አይገደዱም፡፡ ሆኖም በፍርድ ቤቱ የጥቅማጥቅምና የደንብ ልብስ መመሪያ የተፈቀደላቸዉ የፍርድ ቤቱ አስተዳደር ሰራተኞች በስራ ሰዓትና ቦታ የደንብ ልብስ የመልበሰ ግዴታ አለባቸዉ፡፡

11.በዚህ አንቀፅ የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ዳኞች፤ የጉባኤ ተሿሚዎች፤ ዓቃቢያን ህግ፤ጠበቆች፤ ፖሊስ እንዲሁም የፍርድ ቤቱ አስተዳደር ሰራተኞች የችሎቱን ወይም የፍርድ ቤቱን ክብር የሚያቀል ወይም የችሎቱን ስራ የሚያደናቅፍ ወይም የችሎቱን ክብር የማይመጥን በጣም አጫጭር የሆኑ ቀሚሶች፤ሱሪዎች ቁምጣ ወይም ጥብቆዎች ለብሰዉ ችሎት መግባት የተከለከለ ነዉ፡፡

12.የችሎት ታዳሚዎች እንዲሁም ተከራካሪዎች ወንጀል የሚቀሰቅሱ ወይም በዳኝነት ሂደቱ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳርፉ የሚችሉ ጽሁፎች ወይም መፈክሮች ያሉባቸዉን ልብሶች ለብሰዉ ወይም በሰዉነታቸዉ ላይ በመሳል ወይም በመነቀስ በችሎት እንዲታደሙ አይፈቀድም፡፡

ሀ.ማስጠንቀቅያ መስጠት፤

ለ.ለተወሰነ ጊዜ ወደ ችሎት እዳይገባ መከልከል፤

ሐ.ከችሎት ክፍል እንዲወጣ ማድረግ ወይም

መ.በወንጀል፤በፍትሐብሐሄር እና አግባብነት ባለዉ ህግ መሰረት የችሎቱን ስርዓት በመጣስ፤በማወክ ወይም በማደናቀፍ ወንጀል ወዲያዉኑ ፍርድ መስጠትና ቅጣት መወሰን አለበት፡፡

3.የፍርድ ቤቱ አስተዳደር ሰራተኞችና የጉባኤ ተሿሚዎች መመሪያዉን ጥሰዉ ሲገኙ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 መሰረት ዳኛዉ የሚሰጠዉ ዉሳኔ አስተዳደራዊ ተጠያቂነትን አያስቀርም፡፡

## 28. የዳኛዉ ተጠያቂነት

1. ዳኛ ይህን መመሪያ የመፈፀምና የማስፈፀም ኃላፊነት አለበት፡፡

2.ዳኛዉ የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ከጣሰ በክልሉ ዳኞች የስነ-ምግባርና የዲሲፕሊን ክስ ሥነ-ስርአት ደንብ መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## 29. የፍርድ ቤቱ ተቋማዊ ኃለፊነት

ይህን መመሪያ የፍርድ ቤቱ ተቋማዊ ኃላፊነትን በተመለከተ እንደ ፍርድ ቤቱ አቅምና የበጀት ሁኔታ ማሟላት የሚጠበቅበት ሆኖ፡-

1.ይህ መመሪያ ለህብረተሰቡ በመገናኛ ብዙሀን በቴቭዥን ዲስፕሌይ በፅሁፍ ማሳወቅና ግንዛቤ ማስጨበጥ አለበት፡፡

2. ፍርድ ቤቱ የችሎት አዳራሾችን የሚሟላት ኃላፊነት አለበት፡፡

3. የችሎቶችን ስያሜ ፤የዳኞች ቢሮዎች ፤የዳኝነት አገልግሎት መስጫ ክፍሎች በግልፅ ባለጉዳዮች እንዲያቁት ማድረግ አለባቸዉ፡፡

4. የመረጃ ዴስክ አገልግሎት እንዲጠናከር ማድረግ አለባቸዉ፡፡

የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
South Ethiopia Regional State Supreme Court

12. የችሎቱ ፀጥታና ደህንነት ማረጋገጥ አለበት።

**25.የችሎት ደህንነትን ስለማስጠበቅ**

1. ከዳኞች በቀር ማንኛዉም ወደ ፍርድ ቤት ወይም ችሎት አዳራሽ የሚገባ ባለጉዳይ በደህንነት ፍተሻ ሥር የማለፍ ግዴታ አለበት።

2. ማንኛዉም ወደ ችሎት የሚገባ ባለጉዳይ የህግ ባለሙያዎችን ጨምሮ ዱላ፤ስለት ወይም የጦር መሣሪያ ወደ ችሎት ወይም ፍርድ ቤት ግቢ ይዞ መግባት አይችልም።

3.ከላይ የተመለከተዉ ቢኖርም የፖሊስና ማረሚያ ቤት አባላት እስረኞችን ለማጀብ የተሰጣቸዉን ሕጋዊ መሣሪያ እንደያዙ ፍርድ ቤት ግቢ መግባት አይከለከሉም።ሆኖም እነዚህ መሣሪያዎችን ይዘዉ ወደ ችሎት አዳራሽ መግባት አይፈቀድላቸዉም።

**26.የችሎት ማጠናቀቂያ ስርዓት**

1.ዳኛ ወይም ከአንድ ዳኛ በላይ የሆኑ ዳኞች የችሎት ስራዉን ሲያጠናቅቁ ዳኛዉ ወይም የችሎት ሰብሳቢዉ ዳኛ በችሎት ዉስጥ የተገኙትን ሰዎች በማመስገን ጠረጴዛዉን በችሎት መደሻ በመምታት ስለችሎቱ መጠናቀቅ ማሳወቅ አለበት።

2.ችሎት ሲጠናቀቅ የችሎት ስርዓት አስከባሪዉ ወይም ፖሊስ በቅድሚያ ዳኞችን ቀጥሎ በችሎ የተገኙ ባለጉዳዮችን የሰላምታ ምልክት በማሳየት የተገኙ ሰዎችን መሸኘት አለበት።

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**27. ችሎቱ የሚወስዳቸዉ እርምጃዎች**

1.የእርምጃ እና የቅጣት አላማ ሰዉ በፈጸመዉ ጥፋት ተፀፅቶ እራሱን ማስተካከል እንዲችል ማድረግ፤ሌሎች ሰዎችም እንዲማሩበት ማደረግ እና የችሎቱ ክብር እንዲጠበቅ ማድረግ ነዉ

2. የችሎቱን ሥነ ስርዓት በጣሰዉ በማንኛዉም ሰዉ ላይ የችሎቱ ዳኛ የድርጊቱን አፈጻፀም እና ከተፈጸመዉ ጥፋት በስተጀርባ ያለዉን ሃሳብ እንዲሁም ግለሰቡ በህግ ላይ ያለዉን ግንዛቤ ከግምት በማስገባት ወዲያዉኑ የሚከተሉትን እርምጃዎች መዉሰድ ይችላል።

5. በእዉነት ለመተርጎም በገባዉ ቃለ መሀላ መሰረት መተርጎም፤

6. ሌሎችን ፍርድ ቤቱ በሚያወጣዉ የአስተርጓሚዎች መመሪያ መሰረት የተጠቀሱ ተግባራትን መፈፀም አለበት።

## 24. የችሎቱ አስከባሪ ሠራተኛ እና የችሎት ፖሊስ ኃላፊነትና ተግባር

1. ማንኛዉም ሰዉ የችሎት ሥርዓት እንዲያከብር ማድረግ፤ የችሎት ሥርዓት ተጥሶ ሲገኝ ለችሎቱ ዳኛ ማሳወቅ፤

2. ዳኛን ሳይጨምር ወደ ችሎት የሚገቡትን ሰዎች በሙሉ በመፈተሽ ማስገባት፤

3. ዳኞች ወደ ችሎት ከመግባታቸዉ አስቀድሞ የችሎት ባለጉዳዮችን ችሎት ማስገባት፤

4. ችሎቱንና የዳኛዉን/የዳኞችን ስም ለችሎቱ ታዳሚዎች መግለፅ እንዲሁም የችሎቱ ስርዓት ገለፃ ለችሎት ታዳሚዎች መስጠት፤ስልክና ኤሌክትሮኒክስ መሳያዎች ድምፅ እንዲያጠፉ ማሳሰብ፤

5. ዳኛዉ የሚሰጠዉን ትዕዛዝ ማክበር፤ መቀበል እና በአግባቡ መተግበር፤

6. ባለጉዳዮችን፤ምስክሮችን፤ ተከራካሪ ወገኖችን እና ችሎቱን የሚከታተሉ ማናቸዉንም ሰዎች ማክበር፤

7. የችሎት ክርክር በመካሄድ ላይ ሳለ በችሎቱ ካልታዘዘ በስተቀር ጣልቃ በመግባት መናገር ወይም በመንቀሳቀስ የችሎቱ ስራ እንዳይደናቀፍ ወይም እንዳይታወክ ማድረግ፤

8. ለችሎቱ ስራ እጅግ አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር ከዳኞች፤ ከምስክሮች፤ ከባለጉዳዩ እና ችሎቱን ከሚከታተል ከማንኛዉም ሰዉ ጋር አለማዉራት፤

9. ትዕዛዝ እና ዉሳኔ በሚነበበት ጊዜ በአግቡ እንድሰማ የበኩላቸዉን ድርሻ ማበርከት፤

10. ዳኞች ችሎት ሲሰየሙ እና ችሎት አጠናቀዉ ወደ ፅህፈት ቤት ሲሄዱ ተገቢዉን ክብር እንዲያገኙ ማድረግ፤

11. ለዳኛዉ ሊቀርቡ የሚገቡ ሰነዶችን ዳኛዉ ሲፈቅድ ማቅረብ፤

8. እንደ ሻንጣ እና ትላልቅ ቦርሳዎች ወይም ለችሎቱ ስነ-ስርዓት የማይመች ድምጽ መፍጠር የሚችሉ ማንኛውንም እቃዎች ይዞ ወደ ችሎቱ መግባት፣ በማንኛውም መልኩ የችሎቱን ሰላምና ፀጥታ ማወክ የተከለከለ ነው።

## 20. ከዳኞች የሚጠበቅ ስርዓት

1. የችሎቱን ሥነ-ሥርዓት ማክበርና ማስከበር፣
2. የችሎቱ የእለት መዝገብ መዘጋጀቱን፣ ባለጉዳዮች መዘጋጀታቸውን ማረጋገጥ፣ መዛግብትን እንደተቀጠሩበት ቅደም ተከተል የተዘጋጁ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣
3. የስራ ሰዓትን አክብሮ ችሎት መሰየምና መምራት፣ በበቂ ምክንያት ካረፈዱ ባለጉዳዮችን በትህትና ይቅርታ መጠየቅ፣
4. የችሎቱ ሰብሳቢ ዳኛ ወይም ዳኛ ጠረጴዛውን በችሎት መዶሻ በመምታት ችሎቱ ስለመጀመሩ ማብሰር፣
5. ለእለቱ ጉዳይ በቀረቡት መዛግብት ላይ በቂ ዝግጅት ማድረግ፣
6. ዳኛ ችሎቱን ሲመራ የህዝቡን ባህል፣ ወግ እና ሐይማኖት በማክበር መምራት፣
7. ለተከራካሪዎች ወገኖች፣ ለፍርድ ቤቱ አስተዳደር ሰራተኞች፣ ፖሊሶች፣ ለተለያዩ መስሪያ ቤቶች ተወካዮች፣ የችሎት ታዳሚዎች ወይም ለማንኛውም ተገልጋይና ባለጉዳይ ክብር መስጠት እንዲሁም የምስክሮችን መብታቸውን በማክበር እና በእኩልነት ማስተናገድ፣
8. ተከራካሪ ወገኖችን፣ ምስክሮችን እና ሌሎች ችሎቱን የሚከታተሉ ሰዎችን አክብሮት በሚያሳይ መልኩ የሙያ ማእረጋቸውን በመጠቀም፣ አቶ ወይም ወ/ሮ፣ ወ/ሪት ወይም እርስዎ በሚሉት ቃላት መጥራት፣
9. በቀጠሮ እለት ውሣኔ ወይም ትዕዛዝ ካልደረሰ ምክንያቱን ለባለጉዳዮች በመግለጽ ይህንኑ በመዝገብ ላይ በመመዝገብ ጉድለቱ የፍርድ ቤት ወይም የችሎቱ ወይም የዳኛው ከሆነ ይህንኑ ለባለጉዳዮች በመግለጽ በትህትና ይቅርታ መጠየቅ፣
10. ማንኛውም ዳኛ የዳኝነት ፍትሀዊ አካሄድ መርህ በተላበሰ ማንኛውም ባለጉዳይ ሳይሸማቀቅ ሀሳቡን በነጻነት እንዲገልጽ ማድረግ፣
11. ዳኞች ባለጉዳዮችን፣ ጉዳዮችን፣ ህጎችን፣ የዳኝነት ስነ-ምግባር እና የዲስፕሊን ክስ አቀራረብ ደንብ እንዲሁም የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር መመሪያ ድንጋጌዎችን በጠበቀ መልኩ ማስተናገድ አለባቸው።

21. ከባለጉዳዮቹ የሚጠበቅ ስነ-ምግባር

1. የችሎት ባለጉዳዮች የሚከተሉትን መተግበር አለባቸው፡-

ሀ/ በቀጠሮዉ ቀን፤ ቦታና ሰዓት መገኘት፤

ለ/ በችሎት በተዘጋጀላቸዉ ቦታ መቀመጥ፤

ሐ/ በቀጠሮ ቀን ለክርክሩ በአግባቡ ተዘጋጅቶ መቅረብ፤

መ/ ሌላኛዉ ተከራካሪ በሌለበት ከዳኛ ፈቃድ ዉጪ ወደ ዳኛ ቢሮ ያለመግባት፤

ሠ/ ዳኞች በችሎቱ ሲኖሩም ሆነ በማይኖሩበት ጊዜ በችሎት አዳራሽ ዉስጥ የችሎቱን ሥነ-ምግባር ለማስጠበቅ በችሎቱ የሚሰጠዉን የማስከበሪያ ትዕዛዝ ማክበር፤

ረ/ የፍርድ ቤቱ ባለጉዳዮች የሚጠይቁትን ዳኝነት በህጉ አግባብ የፍርድ ቤቱን ሂደት እና አሰራር በማክበር መፈጸም፤

ሰ/ የሚያቀርቡትን ክርክር፤ ተቃዉሞ እና ሃሳብ በሙሉ በግልጽ ለፍርድ ቤቱ ማቅረብ፤

ሸ/ ማንኛዉም ባለጉዳይ ክርክሩን ወይም ጉዳዩን ለዳኛ ሲያቀርብ ወይም ዳኛዉ ሲያናግረዉ ዳኛን ፊት ለፊት መመልከት፤

ቀ/ በችሎት ላይ ተቃዉሞዉን፤ ክርክሩን እና ሁሉንም ሃሳብ ፍትህን፤ እዉነትን እና አግባብነት ያላቸዉን ማስረጃዎች ብቻ መሰረት በማድረግ ማቅረብ፤

በ/ በችሎቱ ክርክር ላይ የዳኛዉን ስም መጥራት ሳያስፈልግ "የተከበረዉ ፍ/ቤት" ወይም "ክቡር ዳኛ" ወይም "ክብርት ዳኛ" በማለት መጥራት፤

ተ/ የችሎቱን ሥነ-ምግባር የማረጋገጥ ግዴታ በቀደምትነት የዳኛዉ ድርሻ ቢሆንም የችሎቱ ስነ-ስርዓት እንዳይጣስ ማድረግ፤

ቸ/ የችሎት ክብር የሚያቃልል ወይም የሚያዉክ ካልሆነ በስተቀር ባለጉዳይ ወይም ተከራካሪ ወገን ሀሳቡን በማይገድብ ተገቢ አካላዊ እንቅስቃሴ በማድረግ መናገር፤

ኀ/ ባለጉዳዩ ችሎቱ ከመጀመሩ በፊት ምስክሮቹ መቅረባቸዉን ማረጋገጥ፤

ነ/ በክስ ወይም በመልስ ከተዘረዘሩት ምስክሮች ጋር በሚጣጣም መልኩ ማንነታቸዉን እና አድራሻቸዉን (የመታወቂያ ወረቀታቸዉን ይዘዉ እንዲቀርቡ በማድረግ) በአግባቡ በማረጋገጥ ማቅረብ፤

ኘ/ ማንኛዉም በያዘዉ ጉዳይ ተከራካሪ የሆነ ሰዉ ምስክሮችን በአግባቡ እና ክብራቸዉን በመጠበቅ ማናገር፤

አ/ ትዕዛዝ፤ብይን ወይም ዉሳኔ በሚነገርበት ጊዜ ወይም ዳኛ እየተናገረ የተቃዉሞ ቃል ሳያሰማ እስከመጨረሻዉ ታግሶ ቅሬታ ያለዉ ከሆነ ጉዳዩ ለሚመለከተዉ አካል ይግባኝ ወይም የችሎቱ አቤቱታ ማቅረብ፤

ከ/ በመጠጥ ስካር ወይም በሱስ ተፅዕኖ ስር ሆኖ ወደ ችሎት መግባት የተከለከለ ነዉ።

ኸ/ ሳል ወይም ጉንፋን ያለበት ባለጉዳይ ሁኔታዉን ለችሎቱ በማሳወቅ በቅድሚያ እንዲስተናገድ መጠየቅ ወይም ከችሎት ዉጭ ሆኖ ተራዉን መጠበቅ፤

ወ/ ከአቅም በላይ በሆነ ጉዳይ፤ ህፃናት የያዙ፤ ነፍሰጡር፤አካል ጉዳተኞች፤አረጋዉያን ችሎቱ በቅድሚያ እንዲያስተናግዳቸዉ ማሳወቅ አለባቸዉ።

**2.ማንኛዉም ባለጉዳይ የሚከተሉትን ተግባራት መፈጸም የተከለከለ ነዉ።**

ሀ. በችሎቱ ዳኛ ክስ፤ ቅጣት፤ዉሳኔ ብይን ወይም ፍርድ መነበብ ወይም ምስክር መስማት ከተጀምረ በኃላ ማንኛዉም ሰዉ ችሎት አቋርጦ መዉጣት፤

ለ. ባለጉዳዩ ወይም ተከራካሪዉ ሀሳቡ እንዳይገደብ ማድረግ እንደተጠበቀ ሆኖ በችሎቱ ዳኛ ችሎት ላይ የተነገሩት ጉዳዩች ትክክል ስለመሆናቸዉ ወይም አለመሆናቸዉ በአይን ምልክት፤ በቅንድብ፤ በፊት ገፅታ ወይም በሌሎች ተገቢነት በሌላቸዉ ወይም አለመስማማትን በሚገልፅ አካላዊ እንቅስቃሴ ማሳየት ወይም ከዳኛዉ ወይም ከችሎቱ ዞር በማለት መናገር፤ ከዳኛ ጋር መሟገት ክልክል ነዉ፤

2.ማንኛዉም ዳኛ መዝገብ ሲቀጥር ጉዳዩ የሚታይበትን ሰዓት፣ቀን እና እንዲሁም ችሎት ለይቶ መግለጽ አለበት፡፡

3.መዝገቡ እልባት ካልተሰጠዉ ወይም ካልተቋጨ ወይም በህግ መሰረት ለጊዜዉ ስለመዘጋቱ በግልፅ በመዝገቡ ላይ ካልሰፈረ በስተቀር በመዝገቡ ላይ ቀጣዩ ሂደት የሚከናወንበትን ቀንና ጊዜ ዳኛዉ ለባለጉዳይ ማሳወቅና በመዝገቡ ላይ ማስፈር አለበት፡፡

**19.በችሎት የተከለከሉ ድርጊቶች**

መንኛዉም ሰዉ ችሎቱ እየተካሄደ እያለ የሚከተሉትን ድርጊቶች መፈጸም ክልክል ነዉ፡፡

1. ዳኛዉ ችሎት እየተካሄደ ችሎቱን በሚያዉክ ሁኔታ ጎኑ ካለዉ ወይም ከሌላ ሰዉ ጋር ድምፅን ከፍ አድርጎ ማውራት፣ መሳቅ፣ በተንቀሳቃሽ ስልክ መነጋገር፣
2. ድምፅ በሚያሰማ፣ እይታን በሚከለክልና የሌሎችን ሰዎች ትኩረት በሚስብ መልኩ ጋዜጣ እና ማንኛውንም ሌሎች ጽሁፎችን በችሎት ማንበብ፣
3. በድምጽ፣ በምልክት ወይም በማንኛውም ሁኔታ ችሎቱን ማወክ ወይም ለክርክሩ አስፈላጊ ያልሆነ ድርጊት መፈፀም፣
4. ከውሀ በስተቀር ሌሎች መጠጦችን መጠጣት፣ መመገብ፣ ጫት መቃም፣ ሲጋራ ማጨስ፣ ማስቲካ ማኘክ፣ መተኛት፣
5. የችሎት ታዳሚዎች በነፃነት የመቀመጥ መብታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ሌላ ሠው እንዳያልፍ በሚከለክል መልኩ እግርን ዘርግቶ መቀመጥ፣ በጠረጴዛ ላይ መቀመጥ፣ ሰው ወደ ችሎቱ እንዳያልፍ በተቀመጡ መከለያዎች ላይ መቀመጥ፣
6. ቃጠሎ የሚፈጥሩ መሳሪያዎችን ይዞ መግባት፣ የጦር መሳሪያ፣ ዱላ ወይም ስለታማ የሆኑ መሳሪያዎችን መያዝ ሆኖም የችሎቱን ሥነ-ሥርዓት አስከባሪ፣ ተጠርጣሪውን ወይም ታሳሪውን ይዞ ወደ ችሎቱ የመጣውን ፖሊስ ወይም በልዩ ችግር ምርኩዝ ዱላ ይዞ የሚንቀሳቀስን አይጨምርም፣
7. ከፍርድ ቤቱ አመራር እና ከዳኛው ፍቃድ ሲሰጣቸው የመገናኛ ብዙሀን ብቻ ችሎቱን በድምፅ፣ በምስል መቅረፅ እንዲሁም ፎቶ ማንሳት እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ሰው ችሎቱን በተንቀሳቃሽ ስልክ፣ በካሜራ ወይም በቪዲዮ ፎቶ ማንሳት፣ ምስል ወይም ድምጽ መቅዳት የተከለከለ ነው፡፡

## 15.ችሎት ስለማክበር

ማንኛዉም የፍርድ ቤቱ ሰራተኛ፤ ፖሊስ፤የችሎቱ ተገልጋይ፤ ተከራካሪ ወይም ባለጉዳይ በሚከተሉት ሁኔታዎች እራሱን ዝግ በማድረግ ለችሎት ያለዉን ክብር ሊያሳይ ይገባል፤

1.ዳኛዉ ችሎት ሲሰየም እና አስችሎ ሲወጣ፤
2.ዳኛው ተሰይሞ ሳለ ወደ ችሎት ሲገባና ሲወጣ፤
3.ማንኛዉም ባለጉዳይ በችሎቱ አቋም ቢስማም ባይስማማም ዳኛዉ ትዕዛዝ፤ ብይን፤ ፍርድና ዉሳኔ አንብቦ ሲያጠናቅቅ፤
4.ዳኞችም ችሎት ሲሰየሙና ችሎት አጠናቀዉ ሲወጡ፤

## 16.የዳኞች መጠሪያ ስያሜ

1.የፍርድ ቤቱ መሪ በማንኛዉም ወቅት እንደ ቅደም ተከተላቸዉ የክብር ስማቸዉን ለሴት **"ክብርት"** ለወንድ **"ክቡር"** በማለት ኃላፊነታቸዉንና ሙሉ ስማቸዉን በመግለፅ ተገቢዉን ክብር በመስጠት ንግግር ሊደረግ ይገባል።

2.ማንኛዉም ሰዉ በችሎት ዉስጥ ወይም ከችሎት ዉጪ ማንኛዉም የክልል ፍርድ ቤት ዳኛን ሲጠራ ለሴት "ክብርት ዳኛ" እንዲሁም ለወንድ "ክቡር ዳኛ"፤ በማለት መጥራት አለበት።

## 17. በግልጽ ችሎት ስለመዳኘት

1.በዝግ ችሎት እንዲታይ በህግ ከተደነገጉት ዉጪ ማንኛዉም ጉዳይ በግልጽ ችሎት መካሄድ አለበት።

2.ማንኛዉም ሰዉ ችሎት ገብቶ የችሎቱን ሂደት የመከታተል መብት አለዉ።ሆኖም የችሎት አዳራሹ በታዳሚ ከሞላ ታዳሚዎች እንደአመጣጣቸው፤የተከራካሪ ቤተሰቦች እንዲሁም እየተካሄደ ባለዉ ክርክር ጉዳዩ የሚመለከታቸዉ በችሎቱ እንዲከታተሉ መደረግ አለበት።

## 18.የቀጠሮ አሰጣጥ ስርዓት

1.ማንኛዉም ዳኛ በክልል ፍርድ ቤቶች በጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር መመሪያ ለጉዳዩ በተቀመጠለት ጊዜ መሰረት መዛግብትን መቅጠር፤ ማስተናገድና ውሳኔ መሰጠት አለበት።

ሐ. በህክምና የተረጋገጠና፣ በልዩ ሁኔታ በችሎቱ ዳኛ ካልተፈቀደ በስተቀር ማንኛዉም የችሎት ባለጉዳይ የህግ ባለሙያዎችን ጨምሮ በችሎት አዳራሽ ዉስጥ መመገብ ወይም ከዉሀ ዉጪ መጠጣት ወይም ማስቲካ ማኘክ፤

መ. በማንኛዉም ሁኔታ በፍርድ ቤቶች ችሎቶች እና አገልግሎት በሚሰጥባቸዉ ክፍሎች ዉስጥ ማንኛዉም ሰዉ ሲጋራ ማጨስ እንዲሁም በፍርድ ቤቱ ቅጥር ግቢ ጫት መቃም፤

ሠ. በፍርድ ቤቱ ቅጥር ግቢ፣በችሎት፣ በዳኞች ጽ/ቤት አካባቢ ዳኞችን በድምጽ ማወክ፤

ረ. ተከራካሪ ወገኖች ሳይፈቀድላቸዉ መናገር በክርክር ጣልቃ መግባት፤

ሰ. ዳኛ በሚናገርበት በማናቸዉም ወቅት ጣልቃ በመግባት ማቋረጥ፤

ሸ.ለችሎቱ ጉዳያቸዉን ሲያስረዱ ለአብዛኛዉ ህብረተሰብ ግልፅነት የሌላቸዉን ቃላት ከመጠቀም መቆጠብ፣ በፍርድ ቤቱ የስራ ቋንቋ አቻ ቃላት ካጣ ችሎቱን ካላስፈቀደ በስተቀር የሌሎች ቋንቋዎች ቃላት መደባለቅ፤

ቀ. በማህበረሰቡ የተለየ ተገቢነት የሌለዉ ትርጓሜ በሚሰጥ ጣትን ወደ ባለጉዳይ ወይም ታዳሚ ላይ እየቀሰሩ ማዉራት ወይም ሀሳብን አካላዊ እንቅስቃሴ በመጠቀም መግለፅ እንደተጠበቀ ሆኖ እጅን ማወናጨፍና ሌሎች ተገቢነት የሌላቸዉን አካላዊ እንቅስቃሴዎች እያደረጉ ማዉራት፤

በ. ማንኛዉም ተከራካሪ ክርክሩን ሲያቀርብ የሌላዉን ወገን ስብዕና ማዋረድ፣ መስፈራራት፤ማሸማቀቅ ዉይም ማንጓጠጥ፤

ተ. ተከራካር ወገኖች በችሎት ዉስጥ በሚደረግ ክርክር ሃሳባቸዉን በቀጥታ ለችሎቱ ከማቅረብ በስተቀር የጎንዮሽ ንግግር ማድረግ

ቸ. ከላይ የተዘረዘሩት መሰል ተግባራትና የስነ-ምግባር ጥሰቶች መፈፀም፣ሕፃናት አስገዳጅ ሁኔታ ከሌለ እና የሕፃናት ማቆያ ሰፍራ በፍርድ ቤቱ ከሌለ በስተቀር ህፃናትን ወደ ችሎት ይዞ መግባት የተከለከለ ነዉ።



5. የጉዳዮች ፍሰት አስተዳዳር መመሪያዎች ላይ የተገለፁ የተቋማዊ ኃላፊነቶችና ተግባራት መፈፀም አለበት፡፡

6. ትልልቅ ንብረቶች፤የጦር መሳሪያዎች የሚቀመጡበት የጥበቃ ቦታ ማዘጋጀት እንዲሁም አሰራር መዘርጋት አለበት፡፡

**30. መሸጋገሪያ ድንጋጌ**

ይህ መመሪያ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከፀደቀበት ከሚያዚያ 7 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**31.መመሪያዉን ስለማሻሻል**

የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘዉ ይህንን መመሪያ ሊያሻሽል ይችላል፡፡

**32. መመሪያዉ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት ከፀደበት ጀምሮ ከሶስት ወር በኋላ የፀና ይሆናል፡፡

**ቦጋለ ፈይሳ ወ/ጊዮርግስ**

**የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚደንት**